# <u>ሰይጣናዊ ቅናት ፤ የተልባ ስፍርና ዘመናዊ ከንቱዎች</u>

*ሀማ ቱማ*

*እጅግም አልከፋኝ ደስም አላለኝ*

*እንደ ተልባ ስፍር በድርባቡ ነኝ ።*

*ያኔ ያኔ በሃቀኛው ትግል ዘመን መንፈሳዊ ቅናት የሚባል ነገር ነበር ። የሚያንብጥ የሚያቃጥል ቅናት ሳይሆን ተመሳሳይ ለማድረግ፤ ለመሆን ቀና ፍላጎትን የሚያንጸባርቅ ። ይህን መንፈስ መያዝ ከባድ ነበር --ለሰው የሚቀናው የሚያቃጥል አሉታዊ ቅናት በመሆኑ ። የዚህን ችግር የተረዱ የዩጋንዳ ባጋንዳ ብሄረሰብ ሽማግሌዎች የሰፈነውን ቅናት ለማዳከም ደግ ስራ ሲያዩ ለመልካም ስራህ ተመስገን ብሎ የመናገር  ብሂል አላቸው ። በኢትዮጵያ ሰፍኖ የቆየው ሰይጣናዊ ቅናት ለመሆኑ ኢትዮጵያን ማንቋሸሽ ከሚቀናው ጠማማ ፕሮፌሰር ሁኔታ ራሱ ሊታይ የሚችል ነው ።*

*ሰይጣናዊ ቅናት እንደ ቅ ኀበጥ ያለ ነው ። ደግ የሰራውን፤የሆነለትን፤ስሙ የተጠራውን፤ ሕዝብንም በጥቅሉ በዘረኝነት የሚጠላ ነው ። ተመክሮ ገብይቶ የሚሻሽል ወይም ሊሻሻል የሚጥር ሳይሆን ለምን እሱ እሷ ይህን ሰሩ ፤ ስማቸው ለምን ተጠራ ወዘተ በሚል ቀንቶ ሊያጠፋቸው፤ሊጎዳቸው ወይም ሊያንኳስሳቸው የሚጥር ነው ።  ወያኔ በኢትዮጵያ ይቀናል ፤ በአማራው ይቀናልና ምላሹ ጥፋት ነው ። የወያኔ ልብ አስመራ ነው፤ ተቀማጭነቱ በአዲስ አበባ ቤት መንግስት ቢሆንም አደዬ አደዬ የሚለው ለመቀሌ፤አድዋና፤ አስመራና  ሐማሴን ነው ። መለስ አስር መጽሃፍ ከማነብ አስር ደቂቃ ከኢሳያስ ጋር ባጠፋ ይበልጥ እማራለሁ አውቃለሁ እንዳለ ልንረሣ አንችልም ። ኤርትራን የነካ ጠላታችን ነው ሲል ሙያተኛው ዋሾ ስብሃት ነጋ የደነፋውንም የምንረሳ አይደለንም ። የሰይጣናዊ ቅናት መስፈን ግልጽ በመሆኑ በበኩሌ በኢሕአፓ ላይ ያለውን ሰፊ አሉታዊ ዘመቻ ከዚህ የምነጥለው አይደለም ። ታሪካቸው የቆሸሸ፤ ህዝብና ሀገር በጠየቀው ትግል ያልተካፈሉ ወይም ሚናቸው አጠያያቂ ወይም የሚወገዝ የሆኑ፤ ጸንቶ የታገለው ይህ ድርጅት ላይ ሰይጣናዊ ቅናትን ያንጸባርቃሉ ። ለሀገር ሲሰዋ ሰው አስጨረሰ ይሉታል፤ ለደረሰበት ጥቃት ሊከላከል ሲነሳ ነጭ ሽብር ጀመረ ብለው የፋሺስቶችን ክስ ያስተጋቡበታል ። ለያልነበረና የማይታወቅን ዘረኝነት ከመ ወያኔ ያጓሩና በኢሕአፓ አመራር አንድም አማራ አልነበረም፤ የነበሩትም ትግሬዎች ድርጅቱን አስጠቁት ብለው አሳፋሪ በሬ ወለደ ውሸታቸውን ያጮኋሉ ። ኢሕአፓ ከምስረታው በፊትም ለብሄረሰብ ስብጥር ተገቢውን ትኩረት ቢሰጥም መሰረቱ ኢትዮጵያዊነትና ፖለቲካዊ አቅዋምና እምነት እንጂ ውልደት አልነበረም ። ታሪክ ይነገር ከተባለ ግን በኢሕአፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ብቻ ሳይሆን በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አማራ፤ትግሬ፤ኦሮሞ ወዘተ አባሎች እንደነበሩበት ታሪክ ይመስክራል ። ይህ ሁሉ ግን በዘር ፖለቲካ የማያምን ለነበረ ድርጅት ቁም ነገር አልነበረም ። ኢሕአፓ አማራዎችም ፤ ኤርትራኖችም፤ትግሬዎችም፤ የኦጋዴን ሶማሌዎችም፤ኦሮሞዎችም፤ ወላይታዎችም አፋሮችም ወዘተ አባሎቹ ስለነበሩ እነዚህን ሁሉ በግንጠላ ሊቃኙ የተነሱ ሀይሎች በኢሕአፓ ላይ ሰይጣናዊ ቅናት አሳድረው ሊያጠቁት ሊያጠፉት ተነስተዋል'፤ሞክረዋልም ። ኢሕ አፓን የመሰረቱት ሀገር ወዳድና ቆራጥ የኢትዮጵያ ልጆች እንጂ የዝቅተኝነትና ሽንፈት ስሜት ያጎበጣቸው የሰው ንዑሶች እንደሚሉት በማንም ባዕድ አልነበረም ። መሰረተ ሰፊ ድርጅት ሆኖ የኦጋዴን ተወላጆች አባሎቹ*

ስለነበሩትም ኢሕአፓ ከሶማሊያ ጋር በነበረው ግንኙነት አንዱ ዋናው ችግር የኦጋዴን ሶማሌዎች የኢሕአፓ አባላት መሆናቸው እንደነበር የሚታወቅ ነው ። ሻዕቢያም ኤርትራዉያን የኢሕአፓ አባል ሊሆኑ አይችሉም በሚል የፈጠረው ችግር ብዙ ጊዜ የተተቸበት ጉዳይ ነው ። ድርጅቱ በሕዝብ ተቀባይነት እያገኘና እየተጠናከረ ሲመጣ በመደገፍ ፈንታ ሰይጣናዊ ቅናት አዝለፍልፏቸው ሊያጠቁት ሊያጠፉት የተሰማሩትን ታሪክ ያውቃቸዋል ። ኢሕአፓ አንዲትም የመከላከያ ጥይት ከመተኮሱ በፊት እስራኤል ያሰለጠነው የነበልባል ጦር ወደ አዲስ አበባ መጥቶ፤ እነ ጌታቸው ሺበሺና አሊ ሙሳ በግድያ ዘመቻ ተሰማርተው ወዘተ በርካታ የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች መገደላቸውን በሚመለከት በበቂ የተዘገበ ጉዳይ ነው ። የድርጅቱ የመከላከል እንቅስቃሴው ደርግ ከፈጀው ከ ሺዎች ዜጋዎች ጋር ሲወደራደር ሊነሳም የሚገባው አይደለም ፡፡ ኢሕአፓ ይወቀስ ከተባለ በበቂ ፋሺስቶችን ከጥቅም ውጪ አለማድረጉና የፋሺስቶቹን ቁንጮ ባለመግደሉ ነው ሊተች የሚገባው ።

የዘንድሮ በሬ ወለደ ደግሞ ድርጅቱን ጸረ አማራ አድርጎ ያቀርበዋል ። ይህ ይታመናል ብለው ሚዳክሩ ቅጥረኞች ሊታዘንላቸው--ግን በጥብቅ ሊወገዙም--ይገባል ። ጸረ አማራው ድርጅት ነው ብዙ ሺ አማራዎችን አደራጅቶና አሰባስቦ በጎጃም ጎንደር ትጥቅ ትግል ለዓመታት ያካሄደው? ሁሉም ሰው ሊያውቅ እንደሚገባው ይህን ሰንካላ ክስ የሚደረድሩት ለመሆኑ አማራው በዚህም በዚያ ሲፈጅ (ደርግም አማራውን አልሳሳለትምና ) የት ነበራችሁ ቢባሉ መልስ የላቸውም ። ወያኔም ቢሆን ፍጅቱንና ጸረ አማራነቱን የጀመረው ገና ለስልጣን ሳይበቃ ነውና ከመቃብር ቦታ በላይ ዝምታን ማን አመጣባችሁ ብለን ልንጠይቃቸው እንገደዳለን ። መንፈሳዊ ቅናት ቢኖርማ ኖሮ ከዚህ ድርጅት በበለጠ ለመታገልና የበለጠም ድል ለማግኘት መፈለግ፤መመኘት ባየለ ነበር ። በቃላት ቦምብና በፈሪ ዘለፋ ሳይሆን በተጨባጭ ተጋድሎ ምን ሊደረግ እንደሚችል ማሳየት በቀደመ ነበር ። የዘመነ ደርጉ ይቅርና የአርባጉጉውን ፍጅት ለምንስ በዝምታ አለፉት ? ይህን ህብረ ብሔራዊና ታጋይ ድርጅት ኮናኞች ግማሾቹ ከጸረ ሕዝብ ደርግ ጋር ያበሩ ቀሪዎቹ ደግሞ እስከትላንት ከወያኔ ጋር--በመቀሌም ጭምር-- ሲጨፍሩ የነበሩ መሆናቸውን መረዳቱ አልከበደንም ። ኢሕአፓ ግን ጸረ ማንም ብሔርና ሕዝብ ሊሆን ቢፈልግም እንኳን መሰረቱ የሚናድበት እንጂ የሚሆንለት አይደለም ። መሰባሰቢያ መሰረቱ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ነበሩና፤ናቸውናም ነው ። ድርጅቱ በኢትዮጵያ ላይ አልቀናም ። ለኢትዮጵያ ቀናላት--ዴምክራሲ፤ዕድገት ብልጽግናን እኩልነትን ተመኘላት እንጂ ። በኢትዮጵያ የቀኑትና ሊያፈርሷት ሊጎዷት የተመኙ እነ ወያኔ ሻዕቢያና ሌሎችም ጠላቶቿዋ ናቸው ።

ለሰው ውድና ክቡር ስጦታው--ሀብቱም ልንል እንችላለን--ህይወቱ ናት ። ከበረም የነጣ ድሀም ሆነ ሁሉም ህይወቱን ይወዳል። ከአንዴ በላይም የኖሩ ሰዎችን ያላየን በመሆኑም ምትክ አልባ ህይወቱን በቀላሉ ወይም በንዝህላልነት የሚያጠፋ አይደለም--ካልታመመ በቀር ። ውድ ህይወትን ለመገበር የሚያበቃ ፍቅርና እምነት ካለ ግን ህይወቱን ሊሰዋ ዝግጁ ይሆናል ብዙ ሰው። ሀገር ወዳድነት በተጨባጭ ይህ ነው ። ሀገሬ ሀገሬ ብሎ ማቅራራትና ሰንደቋን ለብሶ መወዝወዝ ከባድ አይደለም ። የሀገር ፍቅር ሀቀኝነት የሚለካው በትግልና መስዋዕትነት ዝግጁነት ነው ። ሀገርን ካፈቀርን ሀገርን ከጥቃት ለመጠበቅ ውድ ያልነውን ህይወት አሳልፈን ልንሰጥ ዝግጁ መሆን አለብንም ማለት ነው ። ቃል ወዲህ ግብር ወዲያ ከሆነ ግን ለሀገር የሚበጅ ውጤት እንዳማይገኝ ተመክሮ ያስተምረናል ። በፖለቲካ ተልባ ስፍር ይዞታ መርገም ነው ። ታሪካችን በከንቱዎች የታጀበ ነው--አርበኞችና ጀግኖች አኩሪ ምዕራፎችን እንደጻፉት ሁሉ ። ታከለ ስንል ኃይለስላሴ ጉግሳም ብለናል፤ አቡነ ጴጥሮስ ባለ አፋችን አቡነ ጳውሎስ ማለታችንም የሚካድ አይደለም ። መዋለል ዕጣ ክፍሉ የሆነ ዜጋ ሲያምሰን

ባጅቷል ። እዚህ እዚያ የሚረግጠውና የመጣውን ባለነፍጥ ሁሉ ሲደግፍ የቆየው የኢትዮጵያን ታሪክ የከሸፈ ባዮ አዛውንት ፕሮፌሰር--ዕድሜ ሰጧቸው ስህተታቸውን እንዲያዩ እመኛለሁ-- ሌላም ምሳሌ ናቸው ። አስራት ባለ አፋችን መስፍን እንድርያስ ስንልም ተደምጠናልና የትዝብት ሰለባ መሆናችን አያስገርምም ። በኢሕአፓ የታሪክ ሂደት በአያሌው ሊያጠፉት የተነሱት ከንቱዎች በአብዛኛው በታሪኩ የቀኑ፤የትግል ሂደቱ አካል ያልነበሩ፤ በወጣቶቹ ዋናው የሀገር ቤት ትግል ያልተንቀሳቀሱና የቀኑም ናቸው ። ወይም ፈርተው ደንብረውና ለአልባሌዎች ሰግደውና ተገዝተው የከዱት ናቸው ። ራሳቸውን ያውቃሉ ። በድርጅቱ የአቅዋም ጽናት፤ የሕዝብ ተቀባይነት፤ አልበገር ባይነት፤ ሕዝባዊ መሰረትና ዝናም የቀኑ ናቸው ። ይህን ስንል ለጠላቶች ቅጥረኞች ስምሪት ዓይን ጨፍነን አይደለም ። ዛሬ በጸረ ኢሕአፓ ዘመቻ ላይ ያሉት ብዙዎቹ ወይ ወንጀለኞች ወይ የወያኔ ቅጥረኞች ለመሆናቸው ጭቅጭቅ ጠያቂ አይደለም ። ወያኔ ራሱ ጸረ ኢሕአፓነቱ የሚያቃጥል ቅናትና የዝቅተኛነት ስሜትን አዘል ለመሆኑ ምስክር መጥራት የለብንም ። ቢያሰቅቅም ደግሞ የድርጅቱ አባል የነበሩ ኢትዮጵያዊነትን ክደው የወየኑ ወይም የጎጥ አባወራ የሆኑ ማፈሪያዎች መኖራቸውንም መደበቅ መካድ የሚቻል አይደለም ። ድርጅቱ የህብረተሰቡ ውጤት ነው- የጺጋውም የመርገሙም ነጸብራቅ ። ማፈሪያ ኢሕአፓዎች መታየታቸው መጠበቅ ያለበትም ነው ። የነዚህ ዝቅጠት ግን የድርጅቱን አኩሪ ታሪክ የሚያዘቅጥ ሊሆን የሚችል አይደለም ። የቄሱና ሙፍቲህ ጠባይ የህይማኖቱ መመዘኛ አይደለምና ነው ።

ባላውቀውም የሚያስቀኝ አንድ የራዲዮ ዜና ሀተታ አቅራቢ አለ ።በደርግ ጊዜ ዝና ያገኘው በተለይ ስለ ኢራቅ ወረራና ጦርነት ሲያቀርብ በነበረው ዘገባ ነበር ። እሱ ይበል አይበለው ባላውቅም ሳዳም ሁሴን ቡሽንም እተዋለሁ፤ታቸርንም እተዋለሁ ይህን የኢትዮጵያ ጋዜጠኛ ግን አለቀውም ብሏል ይባል ነበር ። ታዲያ ይህ ጋዜጠኛ የኢሕአፓን ታሪክ እያበላሹ የሚጽፉትን በተመለከተ እንጻፍ ካልንማ በሚል የጻፍኳቸውን አጫጭር ትችቶች ጠቅሶ ታሪክ እምናውቀው እኛ ነንና አትጻፉ ይላሉ በሚል በአሉታዊ ተችቶኛል ። አቢይ ነጥቦችን ለማንሳት መንደርደሪያ ሆኖኛልና አመስግነዋለሁ ብልም ትችቱ መሰረተ ቢስ መሆኑን ከመጥቀስ ላልፍ አልችልም ። ስለ ኢሕአፓ አትጻፉ ማለትን የምንችል አይደለም--የማገዱም ፍላጎትም ሙብትም የለንም ። የፈለጉትን ዝባዝንኬ ለመጻፍ መቻላቸውን ነበረ፤የወሬ ነጋሪ፤ የአሲምባ ፍቅሬ፤ ምስክርነት፤የደም ዘመን፤ትግላችን፤ አብዮታችን፤እንቆቅልሽ፤ የተቋረጠ ጉዞ ወዘተ እያሉ የጻፉትን ውጥንቅጥና ሀሰት ሁሉ መጥቀሱ ይበቃል ። አንዳንዶቹ አስመሳዮችማ ራሳቸውን የድርጅቱ አመራር ኮሚቴ አባልም ነበርን ብለው ቀጥፈዋል --ስደት ለወሬ ያመች የለም ማለት እንችላለን ። ገና ታሪካችንን ባንጽፍም ግን አልፎ አልፎ ምነው አበዛችሁት ማለት ሙብታችን መሆኑ መካድ የለበትም። የድርጅቱን ታሪክ እኛ ብቻ ነን የምናውቀው  ይላሉ ለሚለው ያለን መልስ ደግሞ  እንዴታ የሚል ነው ። ታሪካችንን ከእኛ በላይ ማን ሊያውቅ ይጠበቃል ? ድርጅቱን የመሰረቱት አልጄሪያና ምዕራብ ጀርመን ናቸው? -- ቅዠት ! ሻዕቢያ ነው ? ውሸት ። ድርጅቱ የሶማሊያን ወረራ ደገፈ-- የደርግ ቅጥፈት ። መቀጠል ይቻላል ። ታሪክን ማጤን መተንተን ማወቅ ያልቻለው ትውልድ ይህን ሀሰት ሁሉ በአንቀልባ አዝሎ ሊጓዝ መነሳቱ ራሱን ለትዝብት ይዳርገዋልና እንጂ የኢሕአፓን ታሪክ በቅንጣትም ሊያጎድፍ የሚችል አይደለም ። የከንቱዎች ዘመቻ ውድቀት ደግሞ ተደጋግሞ የታየ ነው። ታሪክ የሚጠይቃቸው ዓይናቸውን በጨው አጥበው ያልሆነ ሲተርኩ ወይም ሌሎችን ሲከሱ ሲወነጅሉ ዝምታን ትተን ታሪክ ይወሳ ካልንማ፤እንጻፍ ካልንማ ብለን እርምት ማድረጉ ግዴታችን ይሆናል ። በሕይወት እያለን የደርግ ወንጀለኞች፤ የወያኔ ዘረኛ ነፍሰ ገዳዮችና አረመኔዎች ታሪክን ቀልብሰው ብልግና ትረካቸውን ብረዛቸውን ሲያሰራጩ ዝምታ ሊጠብቅብን አይገባም ። ለዘመናዊ ከንቱዎች ያለን ምላሽ ዝምታ አይደለም ። የተልባ ስፍር ፖለቲካንም አንለግሳቸውም ። ያልደረሰብት ግልግል ያውቃል ተብሏል ። እኛ ስለ ነበሩና ስላሉ አገዛዞች ስናነሳ የፈሰሰ የሕዝባችን ደም ከፊታችን ተደቅኖ ነው ። የአጼው ግፍ ይረሳ ብንል እንኳን ስንቱን በግፍ የፈጀውን አረመኔ ኮለኔልና ደርግ የተባሉትን ወንጀለኞች ልንረሳ አንችልም ። ወያኔ

የፈጀውን ስንት ሺ ልንረሳ አንችልም ። ይህን የመርሳት ችሎታ ያልተሰጠን ነንና ኢትዮጵያ ሀገሬ ስንል ገዳዮችን ማቀፍና ፍቅር መተቃቀፍ የሚለው የቅንጦት ቅዠት መቼም ከቶም የእኛ ሊሆን አይችልም ። ወያኔ ጠላታችን ነው ። የፈሰሰውን ደም ሁሉ መበቀል ደግሞ ግዴታችን ነው ። ሀገር ማዳን ትግሉ ይህን ይጠይቀናል ። በመራራ ኢትዮጵያዊ ጥላቻ ወያኔ ላይ መነሳትና ወያኔን ማውደም። የኢትዮጵያዊነት የወቅቱ ተልዕኮ ይህ ብቻ ነው ።

በወያኔ ላይ አተኩረን ስንታገልና ያለፈውን ወደ ማቀዝቀዣ አስገብተን ወደፊት ልንል ስንነሳ በነሱው በወንጀለኞቹ ብሶ የክህደት ጥርሳቸውን ዳግም አሹለው ሊነክሱን ይወራጫሉ ። የህገር አንድነትና ጥቅምን በማስቀደም ከበቀደም ጠላቶች ጋር ሳይቀር አብረን በግንባር ለመሰለፍ መጣራችን የሚታወስ ነው ። እነሱ ግን ይህን መቀበል አልተቻላቸውም ። ታሪክ መበረዝ ብቻ ሳይህን እንድገና ወኝጀላቸውን ሊኖሩት በመፈለጋቸው ችላ ወደማንልበት ሁኔታ ራሳቸው ከተውናል ። ታሪክ የተረሳም መስሏቸው ሰለባቸውን እያወገዙ የወቅቱንም ትግል መሪ በሉን ብለው ውዥንብርን ሲነዙና ለቀጣሪዎቻቸው ሲታዘዙ በዝምታ ወደማናልፋቸው ደረጃ አድርሰውናል ።እንደ ተልባ ስፍር ፖለቲካቸውን እያራገቡ ወያኔንም ወዳጅ ጠላት እያሉ ትግል ወደፊት ሲል እነሱ ወደ ኋላ እየጎተቱ መገኘታቸውንም ሁላችን አይተናል ። የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት ወያኔና ገንጣዮች የሸረሸሩትን ያህል እነዚህም አዛኝ ቅቤ አንጓች መስለው ጉዳት እያደረሱ በመሆኑ እይታችንን ወደ ትግል ጠሮች ማዞሩ ግዴታ ሆኖብን ተገኝቷል ። ጠላትነታቸውን ከምናውቃቸው ሀይሎች ጋር ተባብረው የሀገር አድኑን ትግል ሲጎዱም በዝምታ ማለፉ ወይም ለከንቱ ባንዳዎች ጆሮ መድረክ መስጠቱ ሊዋጥልን የሚችል አልሆነም ። የሻዕቢያን ሻጥር በተመለከተ ከድርጅቱ በላይም አውቃለሁ የሚል ካለ ዋሾ ነው ልንል እንደፍራለንና በዚህም በኩል ማንም ሊሰብከን ወይም ሊያስተምረን ብቃት ያለው ሆኖ አላገኘንም ። ድርጅቱን ሻዕቢያ ፈጠረው ብሎ በሀገራችን ሰማእት ላይ መሳለቅ የደርግና የወያኔ ቅጥፈትና ኢታሪካዊ ዝባዝንኬ መሆኑ ደግሞ ብዙ ጊዜ የተነገረ፤የተጋለጠ ነው ። እጅግም አልከፋኝ ሳይሆን በአያሌው ከፍቶናል ፤የጠላታችን የወያኔ አገዛዝ መሮናል፤ዘረኝነት አንገፍግፎናል፤የከንቱ ባንዳዎችና አስመሳይ ታጋዮች ሻጥር እጅ እጅ ብሎናል ።ሀቁ ይህ ነው ። ብርጭቆው ግማሽ ሙሉ ግማሽ ባዶ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ባዶ ነው ።

ለሀራችን በእውነቱ የምንቀና ከሆነ ለወያኔ አናድርም፤በጸረ ወያኔዎች ላይ አንዘምትም ። ስንቶቹ ድረ ገጾች የወያኔን ስም ሳያነሱ ግን ነጋ ጠባ ሀገር ወዳድ ድርጅቶችን በመጥረብ ጊዜ እንደሚያጠፉ የምናውቀው ነው ። በሆድ በገንዘብ የተገዙ በሀገር ቅርጫ ሻሞ ሻሞ፤እኔ እኔ ገብተው በቤትና በንግድ ፍቃድ ፤በክልልና ጎጥ ቁልጭልጩም ወያኔ ለራሱ የተለመው የግንጠላ ሂደት ፍንጥቅጣቂው ይመጣልናል በሚል ስንቶቹም የወያኔ አጃቢዎች ሆነው እንደደጎዱም አላጣናውም ። ክብር የሆነውን ኢትዮጵያዊነትም ተወናብደው የተዉት ራሳቸውንም ባዕድ ብለው በሁሉም መስክ ሕዝብችን ያሉትን በሚጎዳ የጥላቻ አማራጭ ተዘፍቀው እነሆ ለወያኔና የሻዕቢያ መጠቀሚያ ሆነው ያሉትንም  ታዝበናል ። ዛሬም በወያኔ ውድቀት ዋዜማ ሚናቸው የተለየ አልሆን ብሎ ለሕዝብ የሚበጀውን ሽግግር ለማደናቀፍ ለወያኔ በጀሌነት ሊሰለፉ አሊያም ከጠላቶች ጋር ሆነው የሕዝብን አንድነት ሊያፈርሱ በመጣር ላይ ናቸው ። ይህን መታገልና ኢትዮጵያን ከጥፋት ማዳን ባለው አገዛዝ ላይ ቅንጣትም ጋት የማይለቅ ያልበረደ ጥላቻ ሊኖረን ያስፈልጋል ። ጥላቻ ትሰብካላችሁ ይሉናል--ታዲያ ሌላ ምን ጠበቃችሁ እንላቸዋለን ።  የወያኔ ጠር ነን ሲሉ ቆይተው ቁርጡ ቀን ሲመጣ ሽብረክ ያሉትና ሰላም ሊሰብኩ የተነሱትን በደፈናው ወያኔ ባንልም በዋና  ይዘታቸው ግን የሕዝብ ትግል ደጋፊዎች አለመሆናቸውን ደፍረን መናገር እንችላለን ። ገና ከመነሻው የተቃወምናቸው ታዋቂ ነን ባዮች ግለሰቦች አለምክንያት አልነበረም ። አንድም ውሳጥቂ መረጃ አግኝተን ወያኔ ጋር ያላቸውን ጥምረት በማወቃችን (ለምሳሌ የኢዴፓ መሪ የነበረው ኋላ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሊጋለጥ የቻለው ከሀዲ) አሊያም በታሪክ የነበራቸውን ሚና በማጤንም ነው ። ለምሳሌ ጵሮፌርሰር መስፍንን ይተቸነው ያለን ሕዝብ የለም ብለው

በመካዳቸውው ብቻ ሳይሆን ለነመለስ ዜናዊ በሰጡት ድጋፍ፤በጃንሆይ ጊዜም በነበራቸው አጠያያቂ ሚናና ከባዕድ ሀገርም ጋር ይዘውት በቆዩት አነጋጋሪ ዝምድና ነው ። ይህ ሐሜት ሳይሆን ለራሳቸውም  በቀጥታ የነገርናቸው ጉዳይ ነው ። የኢዴፓው ሰውየ ከመሰረቱ የወያኔ ጥንሥ መሆኑን ስናጋልጥም ብዙዎች ቀናችሁበት ብለው አውግዘውን ነበር ። በዚህ የደገፍን ዶክተር ታየ ብቻ እንደሆነ ትዝ ይለኛል ። እኛ ግን በግለሰቡ ላይ መንፈሳዊም ሰይጣናዊ ቅናት አልነበረንም -- ተቃውሞ እንጂ ። ከሻዕቢያ ድጋፍን መጠበቅ እናደማያዋጣ ገና ከጠዋቱ አባላችን ለነበረው ለተስፋዬ ጌታቸው የመከርነው ነው ። ባለው ሁኔታ ተጠቅሞመታገል ልሚለው እንግዳ አለነበርንም ። ስንት ጓዶቻችንን ለወያኔ አሳልፎ የሰጠው ሱዳን ከወያኔ ጋር ሲጣል ይህን በመምጠቅም ከሱዳን ጋር ቀርበን የታጠቅ ሀይል ወደ ቁራ አስገብተን ኢአግን መስርተን ታግለን ነበር ። የሻዕቢያን አይሰራም ያልነው በተጨባጭ በዚህም በዚያ ወያኔ የሚጥል ኢትዮጵያዊ ሀይል እንደማይፈልጉ ካረጋገጥን በኋላ ነው ። ቢቆጣጠሩትም አማራም ሆነ ኦሮሞ ሀይል (እነሱ ኢትዮጵያዊ ሳይሆን በብሄረሰብ መፈረጅ ይቀናቸዋልና ) ወድ ስልጣን ወያኔን ጥሎ እንዲደርስ አይፈልጉም ።ኢትዮጵያን መበታተንና መጨፈሪያቸው ማድረግ እንጂ ነጻና ኩሩ ኢትዮጵያን ከቶም አይፈልጉም ። ይህን በማወቃችን ሻዕቢያን ተጠግቶ ወያኔን እዋጋለሁ ማለት ቧልት ነው ስንል ከርመናል ። ባለፉት 26 ዓመታትም ሻዕቢያ ለሀገር ወዳድ ትግላችን ቅንጣትም ደጋፊ አለመሆኑን ለመታዘብ ችለናል ። አሌ የሚሉን ደግሞ ራሳቸውን ለትዝብትና ለከሀደትም ክስ ያቀረቡት ብቻ ናቸው ። ተስፋዬ ጌታቸው፤ኮለኔል ታደሰ፤ ተስፉ፤ወዘተ ተጨባጭ ምስክሮች ናቸው ። ለኢትዮፕያ አንድነት በሚልም በኤርትራ ደማቸውን ያፈሰሱትን ሀገር ወዳዶች ሆኑ ትይዘው ታስረው ግብረ ስየል ተፈጽሞባቸው ያለቁትን ወገኖቻችን የምንረሳቸው አይደሉም ። በደል የደረሰበትንም የኤርትራ ወንድምና እህት የደገፍነው እንጂ አጀሃ በለው ፍጀው ስንልበት አልተደመጥንም ። ሻዕቢያ ግን የወያኔና የገንጣዮች አጋር ሆኖ ከአሶሳ ጀምሮ እስከ ዛሬም በጸረ አማራው የጥቃት ፖለቲካ ዋና አቀንቃኝ ሆኖ ይገኛል ።

ኢሕአፓ ታክቲክና የሚያዋጣ ፖለቲካን ባላማወቁ አከራሪ ሆኖ ተጎድቷል፤እየተጎዳም ነው የሚሉንም አሉ ። ታክቲክ ወይም ጮሌ ዘዴ ሀገርን መካድና አሳልፎ መስጠት ከሆነ እውነትም ድርጅቱ ታክቶክን ማወቅ ተሰኖች ነበር ማለት እንችላለን ። እንደ ወያኔ የኢትዮጵያ ጠላቶች ለባዕዳን ብንሰግድ ኖሮ ለስልጣን ልንበቃ መቻላችን ምንም ጥርጥር አልነበረውም ። በሀገር ወዳድነታን በመጽናታችን የኢትዮጵያ ጠላቶች ሁሉ አልወደዱንም፤አጥቅተውናልም ። ለዚያድ ባሬ አንድ ሶስተኛ ኢትዮጵያ ሶማሊያ ነው ብለን ብንፈርምለት፤ ለሱዳን መሬት ሲጋፋ በማባረር ፈንታ ውሰድ ብንለው ፤አሜሪካ ወያኔን ደግፉችሁ የተወሰኑ ወንበሮች ተቀብላችሁ ግቡ ሲል እሺ ብንል ፡ደቡብ የመን ሆነ ቻይና በሆነ ጊዜ መንግስቱን ደግፎ ብለው ሲገፉን እምቢ ባንል ኖሮ ዛሬ ምናልባትም ኢሕአፓነታችን ተኖ የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በገዢነት መሰየም የምንችልበት ዕድል ነበርለማለት እንችላለን ። ይህ ነው ተቃሚ ታክቲክ ? ወያኔ ስልጣን ከያዘም በኋላ የከደቱ አከላ እንድንሆን ብዙ ሙከራዎችን በእምቢታ የሸኘናቸው ግባችን የሕዝብ መንግስትና የኢትዮጵያ ነጻነት በመሆኑና ድርጅቱን ለግል ስልጣን ለማብቃት ባለመሆኑ ነው ። ይህን መረዳት ያቃታቸው ለታክቲክ ሆነ ዘላቂ ግብ (ስትራተጂ) እንግዳ ላልሆነው ትምህርትን ሊሰጡ ይቃጣሉ ። ለኢሕአፓ መነሻውና መድረሻው የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ነው ። በመሆኑም ከዚህ ውጭና ይህን በተጻረረ ሊንቀሳቀስ ሊስማማ ከቶም የሚቻለው አይደለም/አልነበረም ማለትም እንችላለን ። ድርጅቱን በሀቀና አቅዋሙ ሊተቹትና ሊያጋልጡት ስለማይችሉ ወያኔም ሆነ ሌሎችም የታሪክ ላፒሶች የሀሰት ታሪክ ማቀንቀንና ማቅረብ ግድ ሆኖባቸዋል ። ሀፍረት ለእነሱ!ውርደት በራሳቸው ላይ !

የኢትዮጵያ የአሁኑ ተጨባጭ ሁኔታ የሀገር ወዳዶችን ህብረት የሚጠይቅ መሆኑ ግልጽ ነው ። ህብረት በቅድሚያ ሰፊውን ሕዝብ የሚያስተባብርና የሚያቀናጅ መፈክርን አንግቦ ሕዝብን ማስተባበርን ይመለከታል ። ኢሕአፓ በብዙ የህብረት ጥረቶች ማዕከላዊና የማይናቅ ሚና ሲኖረው ቆይቶ ለግንባሮች ድክመትና መደናቀፍ--ያደረገው ሰፊና ገንቢ አስተዋጾ ተረስቶ--መወቀሱ ስለበዛበት ከግንባር ሂደት ርቆ መቆየቱ የሚታወቅ ነው ። ደንቃራ ሆነብን ያሉትን ድርጅት ትተው ግን ይህ ነው የሚባል የህብረት ግንባር ለማቆም እንዳቃታቸው ደግሞ የታዘበነው ነው ። እንዲያውም የህብረትን መፈጠር የሚያደናቅፉ ራሳቸውን ህብረት ጥምረት የሚሉ ጎጂ ሙከራዎችን ማየት ተገደን ቆይተናል ።ይህ ነው የሚባል ህብረት አለ ብሎለመናገር ሳንታደል የቆየነው እልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነሳ ነው ። አንደኛ ተቅዋዊ ንን ባዮቹ ድርጅትም ተቃዋሚም መሆን ያቃታቸው የይስሙላ ቡድኖች መሆናችው ።ሁለተኛ ህልውና ያለው ጠንኻራ ድርጅት ማዕከል ሆኖ ባለመገኘቱና ሶስተኛ ባዕዳና ወያኔ ህብረት እንድይፈጠር ባደረጉት ቀጣይ ሻጥር ነው ማለት እንችላለን ። የሌሎችን ተመክሮ ስናይ ለህብረት አንድ ጠንካራና አሰባሳቢ ድርጅት መኖሩ ወሳኝ ነው ።ይህን ሚና ለመጫወት የሚችለው ኢሕ አፓ መሆኑን ደግሞ ተጨባጨም ሁኔታ ሆነ ያለፈው ተመክሮ ያረጋግጣል ። ድርጅቶችን ማበላለጥ ሳይሆን (ሁሉም እኩል ድምጽ ይዞ በነበረበት ስብሰቦች ውስጥ ድርጅቱ ሰርቷል) የአሰባሳቢነትና ማዕለል የመሆን ሚና ወስኘቱን ለማሳሰብ ነው ።ዘመናዊ ከንቱዎች ህብረት መሰረትን ባሉ በማግስቱ ሳይቀር ህብረቱ እየፈረሰ ፤ ውህደት የተባለው ፉርሽ እየሆነ፤ በአጉል ተስፋ ምጸት መኖር ተገደን እንደቆየን ሁላችንም የምናውቀው ነው ። ይህን ሁኔታ ለመለወጥ--ጊዜም እያነሰን ስለመጣ-ዋና ህዝባዊ ሀይል ሆኖ የሚገኘው ኢሕአፓ መሆኑን ቢያንስ ወያኔ በመረዳቱ፤ሻዕቢያም በማወቁ ድርጅቱን ለመጉዳት በሁሉም መስክ እንቅስቃሴያቸውን አጧጡፈው ይገኛሉ ። እየተካሄደ ያለውን ጸረ ድርጅት ቅስቀሳና ዘመቻ ያጤኗል! አንዲትም መስመር በወያኔ ላይ ሳይጽፉ ነጋ ጠባ ድርጅቱ ፤አይ የሀሰት ናዳቸውን የሚያወርዱትን ማጤንም ይበቃል ።

ሁሉም ትውልድ በታሪክ ላይ የራሱን አሻራ ይተዋል ። ማህተሙ የሚያኮራም የሚያሳፍርም መሆን መቻሉደግሞ የተፈጥሮ ህግ ነው ። አንስታይን እንዳለው የሰው ጅልነት ማለቂያ የለውም ። ክጅልነት--ማሞ ቂሎነት አልፎ የሰው ልጅ ክፋትም፤ ስግብግብነትና ጭካኔ መለኪያ የለውም ማለት እንችካለን ። ሟቹ ዘረኛ ደጋፊዎቹ ሊሉ እንደሚሞክሩት ብልህ ሰው አልነበረም ። በአንጻሩም የሚሰራውን የማያውቅ ጅል ሰውም አነበረም ። የስልጣን ሂደት ምርጫው ዘረኝነትና እምባገነነት በመሆኑ በውንጀለኛና ጸረ ሕዝብ ጎዳና ነጎደ ፤ ሞትም ገላገለን ። መጥፎ ሀገር አጥፊ ትውልድንም ወክሎ ነበር ማለትም እንችላለን ። በሁሉም ጊዜ ግን የእናት ሆድ ዝንጉርጉር እንዲሉ ጀግናም ባንዳም ሀገራችን ትወልዳለችና በአሁኑ ጊዜም ዘመናዊ ባንዳዎችን-ከንቱዎችንና በዚያውም ለሀገር የሚሰዉ ጀግኖችንም አፍርታለች ። ከንቱዎቹ በራሳቸው፤በኢትዮጵያ፤ በሕዝብ አይ እምነት ጎድሏቸዋልና ሳይታገሉ የተሸነፉ፤እጅ የሰጡና ለክህደትም የቀረቡ ናቸው ። አድርባይነት፤ፍርሓና ተልባ ስፍር መሆን ይገልጻቸዋል ። መዋለል ሳይታገሉ መሸነፍ ። የኢርትዮጵያ ድርጅቶች ሁሉ በወያኔና ሻዕቢያ ተፈጠሩ ብለው የሚያምኑት የሽንፈትና ዝቅተኝነት ስሜት ስለወጠራቸውና ገንጣዮቹ ገዝፈውባቸዋልናም ነው ።ነውናም የታገሉትን በማውገዝ ብስጭታቸውን የተወጡ ይመስላቸዋል ። በደርግና በወያኔ ላይ ከመዝመት ይልቅ እነዚህን አረመኔዎች ቆርጦ የታገለውንና በመታገል ላይ ያለውን ማውገዙ ይቀናቸዋል ።ራስ ጥላቻ ይሏል ይህ ነው ።ትግሉ ሳይጀምር መውደቅ፤መሸነፍ ። ወያኔ ሀገራቸውን የከዱትን የትግራይ ተወላጆችና መሰል ሌሎችንም ይወክላል ። መድረክ ያጣበቡ ቅጥረኞቹም በዚህ ክህደት ተጠቃለው የሚወገዙ ናቸው ። ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ጸረ ወያኔና ኢትዮጵያዊ አቅዋምን ይዞ ለ26 ዓመት የወያኔና ሻዕቢያን ሴራ ሲቋቋም ቆይቷል ። ይህ ነው ለኢትዮጵያ ስርየት ተስፋ የሚሰጠንና ድላችን እንዳይቀማ ጸንተን እንገኝ ብለን ለመጥራት የግድ የሚለን ። ኢሕአፓ ግዳጁን በመወጣት ላይ ነው ።